# በአየር ንብረት ምክንያት የሚፈጠር መዘግየትን የተመለከተ መርሐ ግብር

በክረምት ወራት የተማሪዎችን ደህንነት ጥበቃ ለመጨመር ከሚደረገው ጥረት አንጻር፣ የዴንቨር የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ተለይተው ለታወቁ ትምህርት ቤቶች ያዘጋጀውን በአየር ንብረት ምክንያት የሚፈጠር መዘግየትን የተመለከተ መርሐግብሩን (Weather Delay Schedule) በተመለከተ አንዳንድ ነጥቦችን ሊያስታውስዎት ይፈልጋል። ይህ መርሐ ግብር ከጠዋቱ 8:30 a.m. ወይም በኋላ የሚጀምሩ ትምህርት ቤቶችን ለአንድ ሰዓት እንዲዘገዩ ያደርጋቸዋል። ሌሎች ሁሉም ትምህርት ቤቶች ከመደበኛ የጊዜ መርሐ ግብራቸው ጋር ይቀጥላሉ።

የእርስዎ ቤተሰብ ይህን መረጃ እየተቀበለ ያለው የእርስዎ ልጆች ትምህርት ቤት በአየር ንብረት ምክንያት የሚፈጠር መዘግየትን የተመለከተ መርሐ ግብር ተጽዕኖ ሊያርፍበት የሚችል ትምህርት ቤት ስለሆነ ሊሆን ይችላል። ተለይተው የታወቁ ትምህርት ቤቶችን ሙሉ ዝርዝር ለማግኘት እባክዎ ይህን ይጎብኙ፡- weather.dpsk12.org።

የዚህ በአየር ንብረት ምክንያት የሚፈጠር መዘግየትን የተመለከተ መርሐግብሩን (Weather Delay Schedule) ዓላማ የትምህርት ቤት አውቶብሶች ተማሪዎችን ከያሉበት ለማሳፈር የሚችሉበትን ተጨማሪ ጊዜ ለመስጠት እና በመጥፎ አየር ንብረት ውስጥ ተማሪዎች መጠበቅ ያለባቸውን ጊዜ ለመቀነስ ነው። ትምህርት ቤትን ለመዝጋት ወይም ሰዓቱን ለማዘግየት የሚሰጠው ውሳኔ በዋናው ተቆጣጣሪ የሚወሰን ሲሆን ከውሳኔ ላይ የሚደርሰውም ከ DPS ትራንስፖርት መምሪያ፣ የትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅቶች እና ከአየር ንብረት ትንበያ ቢሮ ተወካዮች በሚሰጠው መረጃ ላይ በመመርኮዝ ነው።

<u>የ DPS ትምህርት ቤቶች ተለይተው ለታወቁ ትምህርት ቤቶች በአየር ንብረት ምክንያት የመዘግየት መርሐ ግብር ከደረሰባቸው፡-</u>

- የጠዋት የትምህርት ቤት አውቶቡሶች በዘገየው መርሐ ግብር መሠረት ይሠራሉ እና ከመደበኛው ልጆችን የማሳፈሪያ ጊዜ 1 ሰዓት በመዘግየት ልጆችን ከየቦታው ማሳፈር ይጀምራሉ። (ለምሳሌ፡- የእርስዎ የጠዋቱ የትምህርት ቤት አውቶቡስ ልጅ ማሳፈሪያ ጊዜው 7:55 a.m. ከሆነ የእርስዎ አውቶብስ ለማሳፈር የሚመጣው በ 8:55 a.m. ላይ ይሆናል ማለት ነው።)
- በእግራቸው፣ በብስክሌት፣ በመኪና ተሳቢ የሚሄዱ ወይም RTD የሚጠቀሙ ተማሪዎች ሌላ ጊዜ ለትምህርት ቤት ከሚወጡበት ሰዓት 1 ሰዓት ቆይተው እንዲወጡ ይበረታታሉ። (ለምሳሌ፡- ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት ለመሄድ ከቤት የሚወጣው 7:45 a.m. ከሆነ፣ አሁን ትምህርት ቤት በሰዓቱ ለመድረስ 8:45 a.m. ላይ ከቤት መውጣት አለበት ማለት ነው።)
- ECE እና መዋዕለ-ሕፃናት፡- የጠዋት (AM) መዋዕለ ሕፃናት አይሰረዝም። በማዘግያ ጊዜው መሠረት የራሳቸውን መርሐ ግብር አስተካክለው ሥራቸውን ይቀጥላሉ። የከሰዓት (PM) ቅድመ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ትምህርት ቤት ይገባሉ እና የአውቶቡስ አገልግሎት በመደበኛ የጊዜ መርሐ ግብራቸው ላይ ይኖራቸዋል።
- ቁርስ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ሲደርሱ እንዲበሉ ይደረጋሉ።

<u>ሁሉም የ DPS ትምህርት ቤቶች በከባድ የአየር ንብረት ምክንያት ከተዘጉ፡-</u>

- የትራንስፖርት አገልግሎት ምንም ዓይነት አውቶቡሶችን አያንቀሳቅስም።
- የመካከለኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ስፖርቶችን የሚያካትቱ፣ ሁሉም ከትምህርት ቤት በኋላ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች፣ ይሰረዛሉ እና ለነዚህ እንቅስቃሴዎች ትራንስፖርት አገልግሎት አይሰጥም።
- ትምህርት ቤት በሚሰረዝበት ጊዜ ለልጅዎ ስለሚሰጡት እንክብካቤ እባክዎ አስፈላጊውን የዕቅድ ዝግጅት ያድርጉ።

<u>የ DPS ትምህርት ቤቶች በከባድ የአየር ንብረት ውስጥ ከተከፈቱ፡-</u>

- ዲስትሪክቱ የተማሪዎችን ደህንነት ለማረጋገጥ ሙሉ ቀን የአየር ንብረቱን ሁኔታ ይቆጣጠራል።
- አስፈላጊው ትራንስፖርት አገልግሎት ይቀርባል። ሆኖም ግን አገልግሎቶች የአውቶቡስ አሽከርካሪ እና የተማሪ ደህንነትን ለማረጋገጥ ሊሻሻሉ ይችላሉ።
- የትራፊክ ሁኔታዎች ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት በሚሄዱበት ጊዜ፣ በልዩ እንቅስቃሴዎች፣ ፕሮግራሞች ወይም ወደ ቤት በሚሄዱበት ጊዜ ተጨማሪ ጊዜ እንዲያጠፉ ሊያስገድዱ ይችላሉ።
- ከባድ የአየር ንብረት በትምህርት ቤት የሥራ ሰዓት ላይ ከጀመረ፣ ተማሪዎች ከመውጫ ሰዓታቸው በፊት መሄድ ካለባቸው አስፈላጊ ውሳኔ ይሰጣል።
- የአውቶቡስ የጉዞ መስመሮች ከሰዓት በኋላ የሚከተሉትን የጉዞ መስመር በመከተል ይሄዳሉ። ባሉት ሁኔታዎች ላይ በመመርኮዝ፣ ወደ ቤት መድረሻ ጊዜዎች የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ።
- ከትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች በኋላ (አትሌቲክስ ዝግጅቶች፣ ማጠናከሪያ ፕሮግራሞች፣ ወዘተ) ሊሻሻሉ ወይም በአየር ንብረቱ የተነሳ ሊሰረዙ ይችላሉ።

<u>ንዴት መረጃ እያገኙ መቆየት ይቻላል፡-</u>

ቀስ በቀስ እየከፋ የሚሄድ የአየር ንብረት ካለ የዲስትሪክት ባለሥልጣናት በ 5 a.m ላይ ውሳኔ ይሰጣሉ። የሚሰጠው ውሳኔ ትምህርት ቤት ሰዓቱን ለማዘግየት ወይም ትምህርት ቤቱን ለመዝጋት ከሆነ፣ የአካባቢ ቴሌቪዥን እና ራዲዮ ጣቢያዎች ወዲያውኑ እንዲያውቁት ይደርጋሉ እና ስለ ትምህርት ቤት ሰዓት መዘግየት ወይም መዘጋት ደጋግመው ማስታወቂያዎችን ያሰራጫሉ በተጨማሪ thedenverchannel.com, 9News.com, kdvr.com እና denver.cbslocal.com መጎብኘት ይችላሉ። ማስታወቂያዎች በስፓኒሽኛ ከጠዋቱ 1150-AM፣ 1280-AM እና 1090-AM. ላይ በራዲዮ ዜና ላይ ይነገራሉ።

Weather.dpsk12.org - ድንገተኛ የትምህርት ቤት መዘጋት ወይም በአየር ንብረት የተነሳ መዘግየት እዚህ ላይ እና በ transportation.dpsk12.org ላይ ወዲያውኑ ይለጠፋሉ።
ማኅበራዊ መገናኛ ብዙሃን - ትምህርት ቤትን ለመዝጋት ወይም ሰዓት ለማዘግየት የሚገለጹ ማስታወቂያዎች በተጨማሪ በ Facebook.com/DenverPublicSchools፣ እንዲሁም @DPSnewsnow እና @ DPSschoolbus በ Twitter ላይ ይለጠፋሉ።
ነጻ የስልክ ደውሎ ማናገሪያ መስመሮች (Hotlines) - እንዲሁም የትምህርት ቤትን መዘጋት ወይም የትምህር ሰዓት መዘግየት የተመለከተ መልእክት በትምህርት ቤቱ የዲስትሪክት የትምህርት ቤት መዝጊያ ነጻ የስልክ መስመር 720-423-3200 ላይ እንዲሁም በ DPS የትራንስፖርት አገልግሎት ነጻ የስልክ መስመር ላይ 720-423-4699 የሚገለጽ ይሆናል።
Bus Bulletin - የትምህርት ቤቱ ቢጫ አውቶቡስ ላይ የሚሳፈሩ ተማሪዎች ስለ ትምህርት ቤት ሰዓት መዘግየት Bus Bulletin. ተብሎ በሚታወቀው አዲስ መሣሪያ አማካይነት እንዲያውቁት ይደረጋሉ። Bus Bulletin ለዴንቨር የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የትራንስፖርት አገልግሎት አዲስ የሆነ ፕሮግራም ሲሆን ለትራንስፖርት አገልግሎት ብቁ የሆኑ ተማሪዎች ወላጆች የእነርሱ የተማሪ ቢጫ የትምህርት ቤት አውቶቡስ አገልግሎትን በተመለከተ መረጃ ይሰጣል። ከኖቨምበር 2015 ጀምሮ ወላጆች አውቶብሶች በድንገተኛ አደጋ ምክንያት ወይም በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት በመዘግየታቸው ከ10 ደቂቃ በላይ ሲዘገዩ በጽሑፍ መልእክት፣ በኢሜይል እና በድምፅ ማሳወቂያዎች በእነርሱ ሞባይል ወይም የድር ጣቢያ መነሻ ገጽ ላይ ወላጆች እንዲያውቁት ይደረጋል። ለተጨማሪ መረጃ transportation.dpsk12.org/bus-bulletin የሚለውን ይጎብኙ።

2090 W. 7th Ave. Denver, CO. 80204
720-423-4600 • transportation.dpsk12.org

DENVER PUBLIC SCHOOLS
Discover a World of Opportunity™

# Bus Bulletin

<u>የቅርብ ጊዜ የአውቶቡስ አጠቃቀም ማሳወቂያዎች</u>

ቢጫ የትምህርት ቤት አውቶቡስ የሚሳፈር ልጅ ካልዎት የዴንቨር የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የትራንስፖርት አገልግሎት የBus Bulletin ፕሮግራም መመዝገብዎን እርግጠኛ ይሁኑ። ይህ አዲስ አገልግሎት ዲስትሪክቱ ስለ እርስዎ ልጅ የአውቶቡስ አገልግሎት ለእርስዎ የእውነተኛ ጊዜ መረጃ እና ትኩስ ዜናዎችን እንዲሰጥዎት ያስችለዋል።  አውቶቡሶች ከ10 ደቂቃ በላይ ሲዘገዩ በጽሑፍ መልእክት፣ በኢሜይል እና/ወይም በድምጽ ማሳወቂያዎች ወላጆች እንዲያውቁት ይደረጋል።

<u>የ Bus Bulletin ጥቅማጥቅሞች:-</u>

- ወላጆች እና ትምህርት ቤቶች ስለ አገልግሎት መዘግየቶች በጽሑፍ መልእክት፣ በስልክ ጥሪ ወይም በኢሜይል ማሳወቂያዎች እንዲደርሱዋቸው ይደረጋል።
- ለዚህ አገልግሎት ምንም ወጪ ማውጣት አያስፈልግም።
- ሁሉም የተማሪ መረጃ በምስጢር የሚያዝ እና ደህንነቱ የሚጠበቅ ሲሆን ለማንም ተላልፎ አይሰጥም። ክብረ ገመና በሚገባ ጥበቃ ይደረግለታል!

<u>ወደ Bus Bulletin ለመድረስ:-</u>

የትራንስፖርት አገልግሎት የማግኘት ተገቢነት ያላቸው ተማሪዎች ወላጆች ከ Bus Bulletin ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት ሲመዘገብ ባለው የስልክ ቁጥር እና ኢሜይል አድራሻ ላይ የሚመረኮዝ ሆኖ በአውቶማቲክ የድምፅ መልእክት እና የኢሜይል ማሳወቂያዎችን ለመቀበል ይመዘገባሉ።

<u>የ Bus Bulletin ቅንብሮችን ወቅታዊ ለማድረግ ወይም ከአገልግሎቱ እንዴት መርጦ መውጣት ይቻላል:-</u>

- እርምጃ 1
  - ወደ የእርስዎ Parent Portal Account በ myportal.dpsk12.org ላይ ተመዝግበው ይግቡ።
  - የ Parent Portal መለያ ከሌልዎት፣ እባክዎ myportal.dpsk12.org ን ይጎብኙ እና የእርስዎን መለያ ለመፍጠር “አጀማመር (Getting Started)” የሚለው ላይ ጠቅ ያድርጉ።
- እርምጃ 2
  - አንድ ጊዜ በመለያ ተመዝግበው ከገቡ በኋላ፣ በመዳሰሺያው ግራ ጎን በኩል ያለውን ትራንስፖርት አገልግሎት (Transportation) የሚለውን አዝራር ጠቅ ያድርጉ እና በመቀጠል Bus Bulletin የሚለው ትር ላይ ጠቅ ያድርጉ። ይህ በአውቶማቲክ ወደ Bus Bulletin የድር ጣቢያ እንዲገቡ ያደርግዎታል።
- እርምጃ 3
  - የእንኳን ደህና መጡ መረጃ (“Welcome Information”) ገጽ ላይ፣ ወደ የእርስዎ መለያ ያምሩ (“Proceed to Your Account”) የሚለውን ጠቅ ያድርጉ እና Bus Bulletin እርስዎን እንዴት እንደሚያሳውቅዎት (በኢሜይል/በጽሑፍ መልእክት/የድምፅ ማሳወቂያ) ወይም እንዴት ከአገልግሎቱ እርስዎ መርጠው እንደሚወጡ ለመምረጥ ትንሽ ጊዜ ያጥፉ። ከአገልግሎቱ መርጦ በመውጣት፣ በ Bus Bulletin ለሚያጋጥሙ የአገልግሎት መዘግየቶች ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እንዲያውቁት አይደረጉም።
- እርምጃ 4
  - ለማሳወቂያዎች የእርስዎን የቋንቋ ምርጫዎችን ወቅታዊ ማድረግዎን እና ማሳወቂያዎችን መቀበል የሚፈልጉበትን ማናቸውም ተጨማሪ የስልክ ቁጥሮች እና የኢሜይል አድራሻዎች ማከልዎን እርግጠኛ ይሁኑ።
    - አዲስ ቁጥር ለማከል፣ ስልክ ቁጥር አክል (“Add Phone Number”) የሚለውን አዝራር ጠቅ ያድርጉ እና በጽሑፍ መልእክት ወይም በድምፅ መልእክት እንዲያውቁት መደረግ እንደሚፈልጉ ከሁለቱ አንዱን ይምረጡ።
    - አዲስ ኢሜይል ለማከል፣ ኢሜይል አድራሻ አክል (“Add Email Address”) የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።
    - የቋንቋ ቅንብሮች የቋንቋ ተቆልቋይ ምናሌውን ጠቅ በማድረግ ሊለወጡ ይችላሉ። የቋንቋ ምርጫዎች እንግሊዝኛ ወይም ስፓኒሽኛን ያካትታሉ።

*ማስታወሻ:- የእርስዎን መረጃ በ Bus Bulletin ላይ ማዘመን የእርስዎን በ Infinite Campusወይም በ Parent Portalላይ ያለ መረጃ አይለውጥም። ወደ Parent Portal መዳረሻ ከሌልዎት፣  የእርስዎን ትምህርት ቤት የመስተንግዶ ክፍል ቢሮ በማነጋገር የእርስዎን መረጃ ወቅታዊ ያድርጉ።